# ከፖለቲካ ሽንፈት ለመላቀቅ
# አሸናፊ ድርጅት መገንባት
# ወሳኝ ነው

*ከዋቻሞ አታሮ*

መሪውና አሸናፊው ኃይል ምንጊዜም ጠንካራ ድርጅትና በውስጡ የተሰባሰቡት የፖለቲካ ባለሙያዎችና በፅኑ የቆሙ ቆራጥ ደጋፊዎች ናቸው። በኢትዮጵያ የተቃውሞ ሁኔታ ላይ እነዚህ አንኳር ወሳኞች ባለመኖራቸው ድሉ ለወያኔ ብቻ እየሆነ ሃያ ዓመት አስቆጥሯል።

አሁን በተቃዋሚ ጎራ የሚታዩት የድርጅት ክሬደንሽያል የሌላቸው ሽንፈት ማጥ ውስጥ እየማቀቁ የሚገኙ ብትንና አናሳን ስብስቦች ናቸው። በዚህ እንቅርት ላይ ደግሞ የፖለቲካ ብቃት፣ የመንግሥትነት ልምድና የትብብር ፍላጐት ማነስ በሽታ በፅኑ ተጸናውቷቸዋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብና በመንግሥታት ዘንድ እውቂያ፣ ትስስርና ተቀባይነት አላደሩም። በአጠቃላይ እንዲያው እንደ ቅጠል ቀለው የሚንሳፈፉ ጫጫታዎች ብቻ ሆነው ይታያሉ።

የተቃውሞ ፖለቲካ የሙያና የልምዱ ባለቤቶች የሆኑትን እስካላሰባሰበና እስካልተጠቀመባቸው ድረስ ጥረቱ የትም ሊደርስ ቀርቶ ከመሬት ተነስቶ ለመቆም እንኳ ወገቡ ስለሚንቀጠቀጥ ተመልሶ ዘጭ እያለ ይወድቃል።

ስለሆነም የእስከዛሬው የተቃዋሚ ጐራ የሃያ ዓመት ጉዞ እንኳን ብሔራዊ ሥልጣን ሊይዝ ቀርቶ አገሪቱን፣ ሕዝቧን፣ አንጡራ ሀብቷን፣ ገንዘቧንና ሌሎች ብሔራዊ ጥቅሞቿን ሊያስከብር ከቶ አልቻለም።

ለኢትዮጵያ፣ ለሕዝቦቿና ለብሔራዊ ጥቅሞቿ ቀዳሚ ትኩረት በመስጠት ለአገርና ለፖለቲካው ሊጠቅሙ የሚችሉትን ሁሉ ከየአቅጣጫው እየፈላለጉ አንድ ወጥ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት ፈጥረው ቢታገሉና ዓለም አቀፋዊ እውቅና ቢያገኙ ኖሮ ዛሬ በኢትዮጵያ የማዕከላዊ መንግሥትና የዲሞክራሲ ባለቤት ሆነው ያ ሁሉ ጉዳት በአገርና በሕዝብ ላይ ባልደረሰ ነበር።

አጥፊ ወያኔ ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎችም ጭምር መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል። በተቃዋሚ ሰፈር ስለአሉ ብቻ በጥፋታቸው አገርና ኢትዮጵያዊነት አንድ ቀን አይጠይቃቸውም ማለት አይደለም።

ወያኔ በስልት የፖለቲካና የፕሮፓጋንዳ አጥንት በወረወረ ቁጥር ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ ውሻ እየተሯሯጡ ያንን ማላመጥና በሳይበር መለፋደድ ፖለቲካ አይደለም።

ፖለቲካ ባለቤትና ባለሙያ አለው። የእስከዛሬዎቹ ተቃዋሚዎች ምድረ የፖለቲካ ተስፈኛ ሁሉ አረብ ሲያነድ አበሻም ያቀጣጥላል ብለው ሲያሽቃብጡ ወያኔ የሕዝብ ብሔራዊ ወኔ የቀሰቀሰ አጀንዳ አንግቶ "በቃ"ን ጭጭ ምጭ አድርጎ ሰለቀጠው።

የፖለቲካ የሥነ-መንግሥትና የድርጅት ሰፊ ልምድና ብቃት ያላቸው እንዲሳተፉ ቢደረግ ኖሮ ድል ገና ድሮ ኢትዮጵያዊነትን ባረጋገጠና አገርን ባዳነ ነበር። ለዚያች እናት አገርና ሕዝብ የምታስቡ ከሆነ ምድረ ተቃዋሚ ስብስቦችና እንዲሁ ዝም ብሎ ሳይገባው አብሮአችሁ የሚባክነው ደጋፊ ሁሉ ራሳችሁን በመስታወት ተመልከቱና ድርጊታችሁን መርምሩ።

ምክንያቱም ሕዝብ ያስገኙት ውጤት የለም አይረቡም ነው የሚላችሁ። አገሪቱ እኰ ተቋርቋሪና ካለችበት ችግር መዘው ሊያወጧትና ነፃ ሊያደርጓት የሚችሉ ግለሰብ ጀግኖች የፖለቲካና የድርጅት ባለሙያዎች አሏት። በዚህ ረገድ ችግር የለባትም። ችግር ቢኖር እስከአሁን በተቃዋሚ ሰፈር ላይ ያለው የማይረባ የፖለቲካ ስብስቦች ሴራ፣ አጥር፣ ስድብ፣ አሉባልታና ከኛ ሌላ ከኛ ወዲህ ማንም አዋቂና ፖለቲከኛ የለም የሚለው ገልቱ ስሜት የከረረ ግብዝነትና የጠላትነት አቋም ነው።

ስለዚህ ለአሸናፊ ድርጅት ግንባታና ለባለሙያዎች መሰባሰብ እኛ እኛ ብቻ ማለቱና ማሰናከሉን ትታችሁ ከሚደረገውና ሊደረግ ከሚችለው ጥረት ጋር መተባበር ያስፈልጋል።

ይህ ካልሆነ ግን ትግሉ ጥንድ ትኩረት እንዲኖረው ይገደዳል።

***በጠንካራ ድርጅት***

***ኢትዮጵያዊነት ያሸንፋል !!***